የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARITGAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፲፫
አዲስ አበባ የካቲት ፳ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

13th Year No.1 3
ADDIS ABABA- 27th February , 2006

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፬፹፪/፲፱፻፺፮ ዓ.ም

የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦት እና የማህበረሰብ መብቶች አዋጅ...ገጽ ፫፻፶፫

CONTENTS

Proclamation No. 482/2006

Access to Genetic Resources and Community Knowledge, and Community Rights Proclamation ..... Page 3353

አዋጅ ቁጥር ፬፹፪/፲፱፻፺፮

የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦትን እና የማህበረሰብ መብቶችን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

ኢትዮጵያ ያላት ከፍተኛ ብዝሀ ህይወት ፀጋ ለሕዝቦቿ ጥቅምና ብልጽግና እንዲውል በአግባቡ መጠበቅና በዘላቂነት ጥቅም ላይ መዋል ያለበት በመሆኑ፣

ብዝሀ ህይወትን በመንከባከብ፣ በማበልፀግና በዘለቂነት በመጠበቅ ረገድ የኢትዮጵያ ማህበረሰቦች ላደረጉት ታሪካዊ አስተዋጽኦ እውቅና መስጠትና ይህንን አስተዋጽኦቸውን እንዲቀጥሉበት ማበረታታት አስፈላጊ በመሆኑ፡

የኢትዮጵያ የብዝሀ ህይወት ኮንቬንሽንን የተቀበለች እና የኮንቬንሽኑንም አርክቦት ህግ እንዲወጣ የሚጠይቅ በመሆኑ፣

የማህበረሰቦች፣ የአርሶ አደሮችንና የዕፅዋት አዳቃዮችን መብት እንዲሁም የሕይታዊ ሀብት አርክቦትን በሚመለከት የወጣውን የአፍሪካ ሞዴል ሕግን ኢትዮጵያ የተቀበለች በመሆኑ፣

PROCLAMATION NO. 482/2006

A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR ACCESS TO GENETIC RESOURCES AND COMMUNITY KNOWLEDGE AND COMMUNITY RIGHT

WHEREAS, the immense biodiversity wealth Ethiopia is endowed with must be conserved and sustainably utilized for the benefit and development of its peoples;

WHEREAS, it is necessary to recognize the historical contribution Ethiopian communities made to the conservation, development and sustainable utilization of biodiversity resources;

WHEREAS, Ethiopia is party to the Convention on Biological Diversity and the Convention requires the enactment of access legislation;

WHEREAS, Ethiopia has agreed to the African Model Law on Community, Farmers' and Plant Breeders' Rights and Access to Biological Resources;

ያንዱ ዋጋ ብር 6.40
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

የጀነቲክ ሀብት እንዲጠበቅና በዘላቂነት ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ የሚያስችልና የኢትዮጵያ ማህበረሰቦች ያዳበሩት ልማዳዊ የጀነቲክ ሀብት ክብካቤና አጠቃቀም ሥርዓት ሊጠበቅና ሊበረታታ የሚገባው በመሆኑ፣

የጀነቲክ ሀብት ክብካቤና አጠቃቀምን በሚመለከት የኢትዮጵያ ማህበረሰቦች ያካበቱትና ያዳበሩት ዕውቀት እውቅና ሊያገኝና ጥበቃ ሊደረግለት እንዲሁም በእነዚህ ማህበረሰቦች ፈቃድና የጥቅም ተከፋይነት በሰፊው ጥቅም ላይ እንዲውል ሊበረታታ የሚገባው በመሆኑ፣

የጀነቲክ ሀብት ጥቅም ላይ እንዲውል በመፍቀዱና ጥቅም ላይ መዋሉ ከሚገኘው ገቢ በመጋራት ረገድ በሚሰጥ ውሳኔ ላይ የአካባቢ ማህበረሰቦች እንዲሳተፉ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

እነዚህን ዓላማዎች በተግባር ለማዋል የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦትና ማህበረሰቦች በጀነቲክ ሀብታቸውና የማህበረሰብ ዕውቀታቸው ላይ ያላቸውን መብት በሕግ መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ /፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

ክፍል አንድ
ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦት እና የማህበረሰብ መብቶች አዋጅ ቁጥር ፬፻፹፪/፲፱፻፺፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ወስጥ፣

፩/ "አርክቦት" ማለት የጀነቲክ ሀብትን ወይም የማህበረሰብ ዕውቀትን መሰብሰብ፣ መውሰድ፣ ማስተላለፍ፣ ወይም መጠቀም ነው፣

፪/ "ሕይወታዊ ሀብት" ማለት ለሰው ልጅ ጠቀሜታ ያለው ወይም ወደፊት ሊኖረው የሚችል የጀነቲክ ሀብት፣ የእዚሁ ሕዋሳት ወይም አካላት ወይም የእርሱ ስብስብ ወይም ማናቸውም የሥርዓት ምህዳር ሕይወት ያለው አካል ነው፣

WHEREAS, it is necessary to protect and encourage the customary use of genetic resources by Ethiopian communities which are relevant to the conservation and sustainable use of the biodiversity resources of the country;

WHEREAS, it is necessary to recognize and protect the knowledge of Ethiopian communities generated and accumulated with respect to the conservation and utilization of genetic resources and promote the wider application of such knowledge with the approval of and sharing benefits by such communities;

WHEREAS, it is necessary to involve communities in the making of decisions concerning the use of genetic resources and community knowledge and sharing of benefits derived from the utilization thereof;

WHEREAS, in order to realize these objectives, it is necessary to determine by law the access to genetic resources and community knowledge, and to provide for the rights of communities over genetic resources and community knowledge

NOW,THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

PART ONE
GENERAL PROVISIONS

1. Short Title

This Proclamation may be cited as "Access to Genetic Resources and Community Knowledge, and Community Rights Proclamation No. 482 /2006."

2. Definitions

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:-

1/ "access" means the collection, acquisition, transfer or use of genetic resources and/or community knowledge;

2/ "biological resource" includes genetic resources, organisms or parts thereof, populations or any other biotic component of ecosystem with actual or potential value for humanity;

፫/ "ተዋጽኦ" ማለት ከሕይወታዊ ሀብት ተለይቶ የወጣ ወይም የተዘጋጀ ውጤት ሲሆን የዕፅዋት ዝርያዎችን፣ ዘይቶችን፣ ዕጣኖችን ሙጫዎችን፣ ፕሮቲንና የመሳሰሉትን ይጨምራል፡

፬/ "ኢዘቦታ" ማለት የጀነቲክ ሀብት በተፈ ጥሮ ከሚ ገኝበት ቦታው ውጪ የሚገኝ በት ሁኔታ ነው፣

፭/ "አሰሳ" ማለት አንድ የጀነቲክ ሀብት መኖሩን ወይም ያለበትን ሁኔታ ለማወቅ በሀገሪቱ ውስጥ የሚደረግ ፍለጋ ነው፣

፮/ "የጀነቲክ ሀብት" ማለት ለሰው ልጅ ጠቀሜታ ያለው ወይም ወደፊት ጠቀ ሜታ ሊኖረው የሚችል የሕይታዊ ሀብ ትን የዘር ባሕሪ የያዘ የጀነቲክ ቁስ ሲሆን ተዋጽኦን ይጨምራል፣

፯/ "ዘቦታ" ማለት የጀነቲክ ሀብት በተፈጥሮ በሚገኝበት አካባቢ ወይም ሥርዓተ ምህዳሩ ውስጥ የሚገኝበት ሁኔታ ነው፣

፰/ "ኢንስቲትዩት" ማለት በአዋጅ ቁጥር ፩፻፳/፲፱፻፺፱/ እንደተሻሻለ/ የተቋቋመው የብዝሀ ሕይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት ነው፣

፱/ "የአካባቢ ማህበረሰብ" ማለት አንድ የጀነቲክ ሀብትን ተንከባክቦ ይዞ የሚገኝ ወይም የአ ንድ የማህበረሰብ ዕውቀት ፈጣሪ የሆነና በኢ ትዮጵያ በአንድ በተወሰነ የመልክዓ ምድራዊ አካባቢ የሚገኝ የሰዎች ስብስብ ነው፣

፲/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፣

፲፩/ "አስቀድሞ ተገንዝቦ የሚሰጥ እሽታ" ማለት የተወሰነ የጀነቲክ ሀብትን ወይም የማህበረሰብ ዕውቀትን ማርከብ የሚፈ ልግ ሰው አርክቦት ከመፈጸሙ በፊት በሚያቀርበው ትክክለኛና የተሟላ መረ ጃን የያዘ የአርክቦት ጥያቄ ላይ በመመ ሥረት ግለሰቡ የጀነቲክ ሀብቱን ወይም የማህበረሰብ ዕውቀትን እንዲያስረክብ ኢንስቲትዩቱ እና የሚመለከተው የአካ ባቢ ማህበረሰብ የሚሰጡት ፈቃድ ነው፣

፲፪/ "አግባብ ያለው ተቋም" ማለት አንድን የጀነቲክ ሀብት ዘርፍ የማስተዳደር ኃላ ፊነት የተሰጠው ወይም በአንድ የጀነቲክ ሀብት ወይም የማህበረሰብ ዕውቀት ዘርፍ ልዩ ዕውቀት ያለው የመንግሥት አካል ነው፣

፲፫/ "መንግሥት" ማለት እንደ አግባቡ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ወይም የክልል መንግሥት ማለት ነው፣

3/ "derivative" mans product extracted or developed from biological resource this may include products such as plant varieties, oils, resigns, gums, chemicals and proteins;

4/ "ex situ" means a condition in which genetic resource is found outside of its natural habitat;

5/ "exploration" means an activity to find out the existence or the status of a given genetic resources;

6/ "genetic resource" means any genetic material of biological resource containing genetic information having actual or potential value for humanity and it including derivatives;

7/ "in situ" means a condition in which genetic resource is found in its natural habitat or ecosystem;

8/ "Institute" means the Institute of Biodiversity Conservation established by Proclamation No. 120/1998 (as amended);

9/ "local community" means a human population living in a distinct geographical area in Ethiopia as a custodian of a given genetic resource or creator of a given community knowledge;

10/ "person" means a natural or juridical person;

11/ "prior informed consent" means the consent given by the Institute and the concerned local community based on an access application containing a complete and accurate access information to a person seeking access to a specified genetic resource or community knowledge;

12/ "relevant institution" means a state organ responsible for administering or having special technical expertise on a specific sector of genetic resources or community knowledge;

13/ "state" means, the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia or its Regional State, as applicable;

፲፬/ "የማህበረሰብ ዕውቀት" ማለት የጀነቲክ ሀብት ማንበርን ወይም መጠቀምን በሚመለከት የአካባቢ ማህበረሰቦች የፈጠሩት ወይም ለዘመናት ያዳበሩት ዕውቀት፣ አሠራር፣ ፈጠራ ወይም ጥበብ ነው::

፲፭/ "ብዝሀ ሕይወት" ማለት በየትኛውም ሥር ዓት ምህዳር በሚገኙ ህይወት ባላቸው ነገሮች መካከል የሚገኙ ተለያይነት ሲሆን፣ ይህም በዝርያዎች ውስጥ፣ ዝር ያዎች እና በሥርአተ-ምህዳሮች መካከል ያለውን ተለያይነት ይጨምራል::

14/ "community knowledge" means knowledge, practices, innovations or technologies created or developed over generations by local communities on the conservation and use of genetic resources.

15/ "Biodiversity" means the variability among living organisms from all sources of ecosystems and the ecological complexes of which they are part; this includes diversity within species, between species and of ecosystems;

፫. ዓ ላ ማ

የዚህ አዋጅ ዓላማ የሀገሪቱ የጀነቲክ ሀብት እና የማህበረሰብ እውቀት ጥቅም ላይ በመዋሉ ከሚገኘው ጥቅም ሀገሪቱና ማህበረሰቦቿ ፍትሐዊና ማዛናዊ የሆነ ድርሻ እንዲያገኙ በማድረግ፣ የብዝሀ ህይወት ሀብት እንዲጠበቅና በዘላቂነት ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ ነው::

3. Objectives

The objective of this Proclamation is to ensure that the country and its communities obtain fair and equitable share from the benefits arising out of the use of genetic resources so as to promote the conservation and sustainable utilization of the country's biodiversity resources;

፬. የተፈጻሚነት ወሰን

፩/ ይህ አዋጅ በዘቦታ ወይም በኢዘቦታ በሚገኙ የጀነቲክ ሀብቶች እና በማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፣

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ድንጋጌ ቢኖርም፣ ይህ አዋጅ ቀጥሎ በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት የለውም፣

ሀ/ የኢትዮጵያ የአካባቢ ማህበረሰቦች ራሳቸው ወይም በመካከላቸው በሚያደርጉት ልማዳዊ የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት ልውውጥና መጠቀም፣ እና

ለ/ የጀነቲክ ሀብቱን መጠቀምን ለማያስከትል ለምግብ ወይም ለመኖ መጠቀምን ለመ ሰለ የተለየ ጠቀሜታ በቀጥታ ለማዋል ሲባል በሚደረግ የሕይወታዊ ሀብት ምርት ግብይት፣

4. Scope of Application

1/ This Proclamation shall apply on access to genetic resources found in in-situ or ex-situ conditions and community knowledge.

2/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, this Proclamation shall not apply to:

a/ the customary use and exchange of genetic resources and community knowledge by and among Ethiopian local communities; and

b/ the sale of produce of biological resources for direct consumption, that do not involve the use of the genetic resource thereof.

፭. ባለቤትነት

፩/ የጀነቲክ ሀብት ባለቤትነት የመንግሥትና የሕዝብ ይሆናል::

፪/ የማህበረሰብ ዕውቀት ባለቤትነት የሚመለ ከተው የአካባቢ ማህበረሰብ ይሆናል::

5. Ownership

1/ The ownership of genetic resources shall be vested in the state and the Ethiopian people.

2/ The ownership of community knowledge shall be vested in the concerned local community.

ክፍል ሁለት
የማህበረሰብ መብቶች መከበር

፮ መሠረቱ

የአካባቢ ማህበረሰቦች በጀነቲክ ሀብታቸውና በማህበረሰብ ዕውቀታቸው ላይ የሚከተሉት መብቶች አሏቸው፣

፩/ በማህበረሰብ ዕውቀታቸው ላይ የሚፈፀም አርክቦትን የመቆጣጠር መብት፣

፪/ የጀነቲክ ሀብታቸውንና የማህበረሰብ ዕውቀታቸውን የመጠቀም ሊገሰስ የማይችል መብት፣

፫/ የጀነቲክ ሀብታቸውና የማህበረሰብ ዕውቀታቸው ጥቅም ላይ በመዋሉ ከሚገኘው ጥቅም የመጋራት መብት::

፯. አርክቦትን የመቆጣጠር መብት

፩/ የአካባቢ ማህበረሰቦች አርክቦትን ለመቆጣጠር ያላቸው መብት የሚከተሉትን ይጨምራል፣

ሀ/ ለማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦት አስቀድሞ ተገንዝቦ የሚሰጥ እሽታ የመስጠት መብት፣

ለ/ አስቀድሞ ተገንዝቦ የሚሰጥ እሽታ እንዲሰጡ በሚጠየቁ ጊዜ የታሰበው የአርክቦት ተግባር የባህላዊና የተፈጥሮ ቅርሶቻቸው ላይ አደጋ የሚፈጥር መስሎ ከታያቸው ፈቃድ የመከልከል መብት፣

ሐ/ ቀደም ሲል ሰጥተውት የነበረው አስቀድሞ ተገንዝቦ የሚሰጥ ፈቃድ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሕይታቸው ወይም በባህላዊና የተፈጥሮ ቅርሶቻቸው ላይ አደጋ ሊያስከትል የሚችል ሆኖ ካገኙት ፈቃዱን የማንሳት ወይም የመገደብ መብት፣

መ/ ኢንስቲትዩቱ የሰጠው የጀነቲክ ሀብት አርክቦት ፈቃድ በባህላዊና የተፈጥሮ ቅርሶቻቸው ላይ አደጋ ሊያስከትል የሚችል ሆኖ ካገኙት ኢንስቲትዩቱ የሰጠው የአርክቦት ፈቃድ ገደብ እንዲደረግበት ወይም እንዲነሳ የመጠየቅ መብት::

PART TWO
PROTECTION OF COMMUNITY RIGHTS

6. Principle

Local communities shall have the following rights over their genetic resources and community knowledge:

1/ the right to regulate the access to their community knowledge;

2/ an inalienable right to use their genetic resources and community knowledge;

3/ the right to share from the benefit arising out of the utilization of their genetic resources and community knowledge.

7. Art. 7. Right to regulate access

1/ The right of local communities to regulate access to their community knowledge shall include the following:

a/ the right to give prior informed consent for access to their community knowledge;

b/ when exercising the right to give prior informed consent, the right to refuse consent when they believe that the intended access will be detrimental to the integrity of their cultural or natural heritages;

c/ the right to withdrew or place restriction on the prior informed consent they have given for access to their community knowledge where they find out that such consent is likely to be detrimental to their socio-economic life or their natural or cultural heritages;

d/ the right to demand the restriction or withdrawal of the prior informed consent given by the Institute for access to their genetic resources where they found out that is likely to be detrimental to their socio-economic life or their natural or cultural heritages;

፪/ የአካባቢ ማህበረሰቦች አስቀድሞ ተገንዝቦ የሚሰጥ እሽታ የሚሰጡበት ሁኔታና ሥርዓት በደንብ ይወሰናል::

፰. የመጠቀም መብት

፩/ የአካባቢ ማህበረሰቦች ለመኖር በሚያደርጉት እንቅስቃሴ የጀነቲክ ሀብታቸውን ወይም የማህበረሰብ ዕውቀታቸውን በልማዳዊ አሠራራቸውና ደንባቸው መሠረት የመጠቀም ወይም በመካከላቸው የመለዋወጥ ሊገሰስ የማይችል መብት አላቸው::

፪/ በአካባቢ ማህበረሰቦች የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀትን የመጠቀምና የመለዋወጥ ባህላዊ ሥርዓት ላይ የሕግ ገደብ አይደረግበትም::

፱. ጥቅም የመጋራት መብት

፩/ የአካባቢ ማህበረሰቦች የማህበረሰብ ዕውቀት ጥቅም ላይ በመዋሉ ከሚገኘው ገቢ ላይ የመጋራት መብት አላቸው፣

፪/ የአካባቢ ማህበረሰቦች የጀነቲክ ሀብታቸው ጥቅም ላይ በመዋሉ ምክንያት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፰/፩/ መሠረት መንግሥት በገንዘብ መልክ ከሚያገኘው ጥቅም ላይ ፶ በመቶ የሚሆነውን የመጋራት መብት ይኖራቸዋል፣

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፪/ መሠረት የሚገኘው ገንዘብ ለሚመለከታቸው የአካባቢው ማህበረሰቦች የጋራ ጥቅም ይውላል፣

፬/ ከአርክቦት ጥቅም መጋራት የሚገኘው ገንዘብ ለአካባቢ ማህበረሰቦች የጋራ ጥቅም የሚውልበት ሥርዓት በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል::

፲. የማህበረሰብ መብቶች አከባበር

፩/ የአካባቢ ማህበረሰቦች በጀነቲክ ሀብታቸውና በማህበረሰብ ዕውቀታቸው ላይ ያላቸው መብት በራሳቸው ልማዳዊ አሠራርና ደንቦች መሠረት ጥበቃ ይደረግለታል፣

፪/ የማህበረሰብ ዕውቀት የሚለየው፣ የሚተረጐመውና የሚረጋገጠው በሚመለከተው የአካባቢ ማህበረሰብ ልማዳዊ አሠራሮችና ደንቦች መሠረት ነው፣

2/ The conditions and the procedure in accordance to which local communities shall give prior informed consent for access to their community knowledge shall be specified by a regulation;

8. Use Right

1/ Local communities shall have an inalienable right to use or exchange among themselves their genetic resources or community knowledge in the course of sustaining their livelihood systems in accordance with their customary practices or norms.

2/ No legal restriction shall be placed on the traditional system of local communities on the use and exchange of genetic resources and community knowledge;

9. Art. 9 Right to share benefit

1/ Local communities shall have the right to share from the benefit arising out of the utilization of their community knowledge;

2/ Local communities shall have the right to obtain 50% of the benefit shared by the state in the form of money from the benefits derived out of the utilization of their genetic resources in accordance with Article 18(1) of this proclamation;

3/ The money obtained pursuant to Sub-Article (1) and (2) of this Article shall be put to the common advantage of the concerned local communities;

4/ The procedure in accordance to which such money shall be used for the common advantage of local communities shall be specified by regulation to be issued under this proclamation.

10. Protection of Community Rights

1/ The rights of local communities over their genetic resources and community knowledge shall be protected as they are enshrined in the customary practices and norms of the concerned communities.

2/ An item of community knowledge shall be identified, interpreted and ascertained in accordance with the customary practices and norma of the concerned local community.

፫/ የማህበረሰብ ዕውቀት ተመዝግቦ አለመገኘቱ በማህበረሰብ መብትነት የሚከበር መሆኑን አያስቀርም፣

፬/ የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት በጽሑፍ ታትሞ መውጣቱ ወይም በቃል መገለጹ ወይም የጀነቲክ ሀብቱ በጅን ባንክ ወይም በሌላ ማናቸውም የማንበሪያ ቦታ ወይም ጥቅም ላይ ውሎ መገኘቱ በማህበረሰብ መብትነት የሚከበር መሆኑን አያስቀርም::

ክፍል ሦስት
አርክቦት ስለሚፈጸምበት ሁኔታ

፲፩. የፈቃድ አስፈላጊነት

፩/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ /፬/ ንዑስ አንቀጽ ፪/ሀ/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ከኢንስቲትዩቱ የአርክቦት ፈቃድ የተሰጠው ካልሆነ በስተቀር ለማናቸውም ሰው የጀነቲክ ሀብት ወይም የማህበረሰብ ዕውቀት ማርከብ የተከለከለ ነው፣

፪/ በግልጽ ተለይቶ ካልተፈቀደ በስተቀር የጀነቲክ ሀብትን ለማርከብ የተሰጠ ፈቃድ ከጀነቲክ ሀብቱ ጋር ተያይዞ የሚገኘውንም የማህበረሰብ ዕውቀት ለማርከብ ፈቃድ እንደተሰጠ አያስቆጥርም:: በተመሳሳይ ሁኔታም የማህበረሰብ ዕውቀት ለማርከብ የተሰጠ ፈቃድ ከዕውቀቱ ጋር ተያይዞ የሚገኘውን የጀነቲክ ሀብት ለማርከብ ፈቃድ እንደተሰጠ አያስቆጥርም፣

፫/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ /፬/ ንዑስ አንቀጽ ፪/ለ/ እንደተጠበቀ ሆኖ ከእንስቲትዩቱ ፈቃድ የተሰጠው ካልሆነ በስተቀር ለማናቸውም ሰው የጀነቲክ ሀብት ከሀገር ማስወጣት የተከለከለ ነው

፬/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ድንጋጌ ቢኖርም የጀነቲክ ሀብትን ለመጠበቅ በሕግ ኃላፊነት የተሰጣቸው የመንግሥት አካላት ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ጀነቲክ ሀብት ወይም የማህበረሰብ ዕውቀት ለመሰብሰብ ከኢንስቲትዩቱ የአርክቦት ፈቃድ ማግኘት አያስፈልጋቸውም፣ ሆኖም ከኢንስቲትዩቱ ፈቃድ ካላገኙ በስተቀር የጀነቲክ ሀብቱን ለሌላ ሰው ማስተላለፍ ወይም ከሀገር ማስወጣት አይችሉም:: የእነዚህ መንግሥታዊ አካለት ሠራተኞች የጀነቲክ ሀብት አርክቦት በሚፈጽሙበት ጊዜ አርክቦት የሚፈጽሙ መሆናቸውን የሚገልጽ ደብዳቤ መያዝ ይገባቸዋል::

3/ The non-registration of any community knowledge shall not render it unprotected by community rights.

4/ The publication or oral description of a given genetic resource or community knowledge, or the presence of the genetic resources in gene bank or any other conservation center or that it is in use shall not affect its protection as community rights.

PART THREE
CONDITION OF ACCESS

11. Requirement of Permit

1/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article 2(a) of Article 4 of this Proclamation, no person shall access genetic resources or community knowledge unless in possession of written access permit granted by the Institute based on prior informed consent.

2/ Unless otherwise explicitly expressed, the granting of permit to access genetic resources shall not be construed to constitute permit to access the community knowledge associated therewith and vice versa.

3/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article 2(b) of Article 4 of this Proclamation., no person shall export genetic resources out of Ethiopia unless in possession of permit granted by the Institute to this effect .

4/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article organs of the state which are empowered by law to conserve genetic resources may not be required to obtain access permit from the Institute to collect genetic resource or community knowledge in the discharge of their duties; provided however, that they shall not transfer the genetic resources or community knowledge to third persons or export same out of Ethiopia unless they are given explicit permit by the Institute, While collecting genetic resources and community knowledge, employees of such institutions must carry with them a letter to this effect.

፲፪. የአርክቦት መሠረታዊ ቅድመ ሁኔታዎች

፩/ የጀነቲክ ሀብትን ለማርከብ በቅድሚያ የኢንስቲትዩቱን አስቀድሞ ተገንዝቦ የሚሰጥ እሽታ ማግኘት ያስፈልጋል፣

፪/ የማህበረሰብ ዕውቀትን ለማርከብ በቅድሚያ የሚመለከተውን የአካባቢ ማህበረሰብ አስቀድሞ ተገንዝቦ የሚሰጥ እሽታ ማግኘት ያስፈልጋል፣

፫/ የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀትን በመጠቀም ከሚገኘው ገቢ መንግሥትና የሚመለከተው የአካባቢ ማህበረሰብ ፍትሐዊና ሚዛናዊ የሆነ ጥቅም ማግኘት አለባቸው፣

፬/ የውጭ ሀገር ዜጋ የሆነ አርክቦት ጠያቂ የሀገሩ ወይም የሚኖርበት ሀገር አግባብ ያለው ባለሥልጣን አመልካቹ የሚኖሩበትን የአርክቦት ግዴታዎች በዚያ ሀገር የሚያስከብርና የሚያስፈጽም መሆኑን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርበታል፣

፭/ አርክቦት የሚፈጸመው በውጭ ሀገር ዜጋ በሆነ ጊዜ የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀትን መሰብሰቡ የሚከናወነው የኢንስ ቲትዩቱ ወይም ኢንስቲትዩቱ የሚወክለው አግባብ ያለው ተቋም ባለሙያዎች በተሳታ ፊነት በተገኙበት መሆን አለበት፣

፮/ የማይቻል እስካልሆነ ድረስ በአርክቦት በተገኘ የጀነቲክ ሀብት ላይ የሚካሄድ ምርምር በኢ ትዮጵያ ውስጥና ኢንስቲትዩቱ የሚመድ ባቸው ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች በሚሳተ ፉበት ሁኔታ መካሄድ አለበት፣

፯/ በአርክቦት በተገኘው የጀነቲክ ሀብት ላይ የሚካሄደው ምርምር ከኢትዮጵያ ውጪ እንዲካሄድ በሚፈቀድበት ጊዜ ምርምሩን የደገፈው ወይም ምርምሩ የሚካሄድበት ተቋም አርካቢውና ተቋሙ የአርክቦት ግዴታ ዎችን የሚያከብሩ ለመሆናቸው ማረጋገጫ መስጠት አለበት::

፲፫. አርክቦት የሚከለከልባቸው ሁኔታዎች

የሚከተሉት ሁኔታዎች በሚያጋጥሙበት ጊዜ ኢንስቲትዩቱ የአርክቦት ፈቃድ ለመከልከል ይችላል፣

፩/ የቀረበው የአርክቦት ጥያቄ ዝርያው የተመና መነን የጀነቲክ ሀብት የሚመለከት ከሆነ፣

12. Basic Pre-Conditions of Access

1/ Access to genetic resources shall be subject to the prior informed consent of the Institute.

2/ Access to community knowledge shall be subject to the prior informed consent of the concerned local community.

3/ The state and the concerned local community shall obtain fair and equitable share from benefits arising out of the utilization of genetic resources and community knowledge accessed.

4/ An access applicant who is a foreigner shall present a letter from the competent authority of his national state or that of his domicile assuring that it shall uphold and enforce the access obligations the applicant.

5/ In cases of access by foreigners, the collection of genetic resources and community knowledge shall be accompanied by the personnel of the Institute or the personnel of the relevant institution to be designated by the Institute.

6/ The research based on the genetic resources accessed shall be carried out in Ethiopia and with the participation of Ethiopian nationals designated by the Institute, unless where it is impossible.

7/ Where the research based on the genetic resources accessed is permitted to be carried out abroad, the institution sponsoring and/or hosting the research shall give a letter of assurance that they shall observe the access obligations attached thereto.

13. Conditions for Denial of Access

The Institute may deny access to genetic resources; where:

1/ the access requested is in relation to the genetic resource of an endangered species;

፪/ አርክቦቱ በሰው ጤና ወይም በአካባቢው ማህበረሰብ ባሕላዊ እሴት ላይ ጉጂ ተጽዕኖ የሚያስከትል ከሆነ፣

፫/ አርክቦቱ በአካባቢ ላይ ያልተፈለገ ጎጂ ተጽዕኖ የሚያስከትል ከሆነ፣

፬/ አርክቦቱ የሥርዓተ ምህዳር መጥፋት አደጋን የሚያስከትል ከሆነ፣

፭/ አርክቦቱ የጀነቲክ ሀብትን የኢትዮጵያን ብሔራዊ ሕግ ወይም ኢትዮጵያ ያፀደቀችውን ዓለም አቀፍ ስምምነት ተጻራሪ ለሆነ ዓላማ ጥቅም ላይ ለማዋል ከሆነ፣

፮/ አርክቦት ጠያቂው ቀደም ሲል የአርክቦት ቅድመ ሁኔታዎችን ወይም የአርክቦት ውሎችን የጣሰ እንደሆነ::

፲፬. የአርክቦት ፈቃድ ስለመስጠት

፩/ የጀነቲክ ሀብት ወይም የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦት ፈቃድ ማግኘት የሚፈልግ ሰው የአርክቦት ማመልከቻ በጽሑፍ ኢንስቲትዩቱ ማቅረብ አለበት:: የአርክቦት ማመልከቻው የሚቀርብበትና ውሳኔ የሚሰጥበት ሁኔታና ሥርዓት በደንብ ይወሰናል፣

፪/ ኢንስቲትዩቱ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ላይ በመመሥረት የጀነቲክ አርክቦት ውል ተደራድሮ ይፈራረማል:: የአርክቦት ውል ሲፈረምም ኢንስቲትዩቱ የአርክቦት ፈቃድ ለጠያቂው ይሰጣል:: ፈቃዱ የአርክቦቱን ዓላማ የሚገልጽና በአርክቦቱ የሚገኘውን የጀነቲክ ሀብት ከሀገር ለማስወጣት የተፈቀደ መሆን አለመሆኑን የሚያሳይ መሆን አለበት፣

፫/ የአርክቦት ጥያቄው የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦትን የሚጨምር በሆነ ጊዜ ኢንስቲትዩቱ የሚመለከተው የአካባቢ ማህበረሰብ የሰጠው አስቀድሞ ተገንዝቦ የሚሰጥ እሽታ ላይ በመመስረት የአርክቦት ውል ተደራድሮ ይፈርማል፣

፬/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፪/፭/ የተደነገገው ቅድመ ሁኔታ የተሟላ ካልሆነ በስተቀር የጀነቲክ ሀብት ከሀገር እንዲወጣ ፈቃድ አይሰጥም::

2/ the access may have adverse effects upon human health or the cultural values of the local community;

3/ the access may cause undersirable impact on the environment;

4/ the access may cause danger of loss of ecosystem;

5/ the access is intended to use genetic resources for purposes contrary to the national laws of Ethiopia or the international treaties to which Ethiopia is a party;

6/ the applicant has violated hitherto access conditions or access agreements.

14. Issuance of Access Permit

1/ A person who wants to obtain permit to access genetic resources or community knowledge shall present an application in writing to the Institute. The conditions and procedure in accordance with which access applications shall be presented examined and prior informed consent shall be given shall be specified by regulations.

2/ Upon giving of prior informed consent, the Institute shall, based on the provisions of this proclamation, negotiate and conclude genetic resources acess agreement.

3/ Where the access application involves access to community knowledge, the Institute shall negotiate and conclude the access agreement based on the prior informed consent of the concerned local community to that effect.

4/ The Institute shall not grant permit for exporting genetic resources out of Ethiopia unless the condition provided under Article 12(6) of this Proclamation is met.

፲፭. የተለየ የአርክቦት ፈቃድ

፩ ኢንስቲትዩቱ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተደነገገውን ሥርዓት በጥብቅ መከተል ሳያስፈልገው የመንግሥት የምርምር ተቋማት፣ ሀገራዊ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና በኢትዮጵያ የሚገኙ የበይነ መንግሥታት የምርምር ተቋማት በሀገር ውስጥ ለሚያካሄዱት የልማትና የአካዳሚ ምርምር ሥራ የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት በቀላሉ ማግኘት እንዲችሉ የተለየ የአርክቦት ፈቃድ ሊሰጣቸው ይችላል:: ሆኖም የተለየ የአርክቦት ፈቃድ የሚሰጣቸው ተቋማት አርክቦቱን በሚፈጽሙበት ጊዜ የሚኖርባቸውን ግዴታዎች ኢንስቲትዩቱ እንደአግባብነቱ ይወስናል፣

፪/ የኢትዮጵያ አባል በመሆን ባፀደቀችው የባለ ብዙ ወገን የአርክቦት ሥርዓት መሠረት የሚደረግ የጀነቲክ ሀብት አርክቦት በባለ ብዙ ወገን የአርክቦት ሥርዓቱ በተገለፀው ሁኔታና ሥርዓት መሠረት ይፈፅማል:: የባለ ብዙ ወገን የአርክቦት ሥርዓት አፈጻጸም የሚመራበት ሁኔታ በደንብ ይወሰናል::

፲፮. የአርክቦት ውል ይዘት

የአርክቦት ውል የሚከተሉትን ጉዳዮች መያዝ አለበት፣

፩/ የአርክቦት ውሉ ተዋዋይ ወገኖችን ማንነት፣

፪/ ለማርከብ የተፈቀደውን የጀነቲክ ሀብት ዓይትና መጠን፣

፫/ ለማርከብ የተፈቀደውን ወይም ለማርከብ ከተፈቀደው የጀነቲክ ሀብት ጋር ተያይዞ የሚገኘውን የማህበረሰብ ዕውቀት መግለጫ፣

፬/ የጀነቲክ ሀብት ወይም የማህበረሰብ ዕውቀቱ የሚሰበሰብበት አካባቢ ወይም ይህንኑ የሚያቀርበው ሰው፣

፭/ ለማርከብ የተፈቀደው የጀነቲክ ሀብት ናሙና እና የማህበረሰብ ዕውቀት መግለጫ የሚቀመጥበትን ተቋም፣

፮/ ለማርከብ የተፈቀደው የጀነቲክ ሀብት ወይም የማህበረሰብ ዕውቀት ሊውል የታሰበበት አገልግሎት፣

፯/ የአርክቦት ውሉ በተጠቀሰው የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት ላይ በወቅቱ ካሉ ወይም ወደፊት ከሚፈጸሙ የአርክቦት ውሎች ጋር የሚኖረው ግንኙነት ምን እንደሚሆን፣

15. Special Access Permit

1/ The Institute may, without the need to strictly follow the access procedure provided for in this Proclamation, grant specific access permit to Ethiopia national public research and higher learning institutions and intergovernmental institutions based in the country, so that they have facilitated access to genetic resources and community knowledge for purpose of development and academic research activities they undertake within the country. When the Institute grants specific access permits to such institutions, it shall determine, as appropriate, the obligations they shall have while having access under such permit.

2/ An access to genetic resources under a multilateral system of access to which Ethiopia is a prty shall be made in accordance with the conditions and procedure specified thereof. The condition and procedure in accordance with which access to genetic resources under multilateral systems shall be implemented shall be determined by regulations.

16. Contents of Access Agreement

An access agreement shall specify, among other things, the following issues:

1/ the identity of the parties to the agreement;

2/ the type and quantitative description of the genetic resource permitted to be accessed;

3/ the description of the community knowledge permitted to be accessed or associated with the genetic resource to be accessed;

4/ the locality where the genetic resource or community knowledge is to be collected or the person providing same;

5/ the institution with which the sample of the genetic resource and the description of community knowledge accessed shall be deposited;

6/ the intended use the genetic resource or community knowledge;

7/ the relationship of the access agreement with existing or future access agreements on the same genetic resource or community knowledge;

፰/ የጀነቲክ ሀብቱን በመሰብሰብ ወይም በጀነቲክ ሀብቱ ላይ በሚደረገው ምርምር ላይ እንዲሳተፍና የአርክቦት ውሉን አፈጻጸም እንዲቆጣጠር ኢንስቲትዩቱ የወከለው አግባብነት ያለው ተቋም የቱ እንደሆነ፣

፱/ መንግሥት ከጀነቲክ ሀብት አርክቦቱ የሚያገኘውን ጥቅም፣

፲/ የአርክቦት ውሉ የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦትን የሚጨምር በሆነ ጊዜ የአካባቢ ማህበረሰቡ ከዚሁ የሚያገኘውን ጥቅም፣

፲፩/ የአርክቦት ውሉ የሚቆይበት ዘመን፣

፲፪/ አለመግባባቶች የሚፈቱበት መንገድ፣ እና

፲፫/ የአርክቦት ባለፈቃዱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚኖሩት ግዴታዎች፣

፲፯. የአርክቦት ባለፈቃድ ግዴታዎች

የአርክቦት ፈቃድ የተሰጠው ሰው የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፣

፩/ የአርክቦት ፈቃዱን ቅጂ የጀነቲክ ሀብቱ በሚሰበሰብበት አካባቢ ላለው ወረዳ አግባብነት ያለው አካል የመስጠትና በተጠየቀ ጊዜም የአርክቦት ፈቃዱን የማሳየት፣

፪/ የጀነቲክ ሀብት በሚሰበሰብበት ጊዜ የገበሬዎችን ዘር ወይም የዱር በቀል ዝርያዎችን ክምችት እንዲመናመን ያለማድረግ ወይም ከጀነቲክ ክምችት ውስጥ ከፍተኛ መጠን ያለውን የጀነቲክ ሀብት ተለያይነት ያለመውሰድ፣

፫/ ከጥብቅ ቦታዎች የጀነቲክ ሀብት በሚሰበሰብበት ወቅት የጥብቅ ቦታዎችን አስተዳደር ደንቦች የማክበር፣

፬/ የተሰበሰበውን የጀነቲክ ሀብት ናሙና፣ አሰባሰብ መረጃና የማህበረሰብ ዕውቀት መግለጫን በኢንስቲትዩቱ ወይም ኢንስቲትዩቱ በሚሰይመው አግባብነት ያለው ተቋም ዘንድ እንዲቀመጥ የማድረግ፣

፭/ ለማርከብ ከተፈቀደለት የጀነቲክ ሀብት ዓይትና መጠን ያለማለፍ፣

፮/ ኢንስቲትዩቱ ሲጠይቀው በአርክቦት ከወሰደው የጀነቲክ ሀብት ላይ ናሙና እና የማህበረሰብ ዕውቀት ቅጅ የመስጠት፣

8/ the relevant institution designated by the Institute to participate in the collection of and/or the research based on the genetic resource to be accessed and be in charge of monitoring the implementation of the access agreement;

9/ the benefit the state shall get from the access to genetic resources;

10/ where the agreement involves access to community knowledge, the benefit the concerned local community shall obtain from the use thereof;

11/ the duration of the access agreement;

12/ dispute settlement mechanisms; and

13/ the obligations the access permit holder shall have under this Proclamation.

17. Obligations of Access Permit Holder

A person who shall be given an access permit shall have the following obligations:

1/ deposit the copy of the access permit granted to him with the relevant regional institution in the district where the genetic resource is to be collected and show the access permit up on request;

2/ not deplete population of farmers planting stock or wild species or to remove significant genetic variation from local gene pool during collection;

3/ Where the genetic resource is to be collected from protected areas, to observe the rules and regulations of the administration of the protected area;

4/ deposit the sample of the genetic resources collected and the collection data, and the description of community knowledge accessed with the Institute or the relevant institution the Institute may designate;

5/ observe the type and quantitative limits of the genetic resource permitted to access:

6/ upon request, supply to the Institute a sample from the genetic resource and copy of the description of the community knowledge accessed;

፯/ ምርምሩ ስለሚገኝበት ደረጃ በመደበኛ ሁኔታ ለኢንስቲትዩቱ ሪፖርት የማቅረብና የጀነቲክ ሀብት በተደጋጋሚ የሚሰበሰብ ከሆነ ስለሚደርሰው የአካባቢ፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጽዕኖ በመከታተል ለኢንስቲትዩቱ ሪፖርት የማቅረብ፣

፰/ ከምርምሩ የተገኙ ውጤቶችንና የተወሰደው የጀነቲክ ሀብት ከምን እንደደረሰ ለኢንስቲትዩቱ በጽሑፍ ማሳወቅ፣

፱/ ለኢንስቲትዩቱ አሳውቆ በጽሁፍ ፈቃድ ሳያገኝ በአርክቦት የተገኘን የጀነቲክ ሀብት ወይም ማህበረሰብ ዕውቀት ለሌላ ሦስተኛ ወገን አሳልፎ ያለመስጠት ወይም እንዲውል ከተፈቀደው የአገልግሎት ዓላማ ውጪ ለሆነ ጉዳይ ያለመጠቀም፣

፲/ የታቀደው ምርምር ወይም የአርክቦት ስም ምነቱ ሲቋረጥ በጥቅም ላይ ያልዋለውን የጀነቲክ ሀብት ለኢንስቲትዩቱ የመመለስ፣

፲፩/ ለኢንስቲትዩቱ አሳውቆ ፈቃድ ሳያገኝ የአርክቦት ፈቃዱን ወይም ከፈቃዱ የሚመነጨውን መብትና ግዴታ ለሦስተኛ ወገን ያለማስተላለፍ፣

፲፪/ በአርክቦት በተገኘው የጀነቲክ ሀብት ወይም የጀነቲክ ሀብቱ አካል በሆነ ነገር ላይ ማናቸውም የአእምሮአዊ ንብረት መብት ለማግኘት ሲፈለግ አግባብ ያለው የኢትዮጵያ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ከኢንስቲትዩቱ ጋር አዲስ ውል የመዋዋል፣

፲፫/ ከኢንስቲትዩቱ ግልጽ ፈቃድ ሳይሰጥ በአርክቦት በተገኘ የማህበረሰብ ዕውቀት ላይ ፓተንት ወይም ሌላ ማናቸውም ዓይነት የአእምሮአዊ ንብረት ጥበቃ ለማግኘት ያለመጠየቅ፣

፲፬/ በአርክቦት የተገኘውን ጀነቲክ ሀብት ወይም የማህበረሰብ ዕውቀት በመጠቀም ለተገኘ የምርት ውጤት የአእምሮአዊ ንብረት ጥበቃ ለማግኘት በሚቀርብ ማመልከቻ ውስጥ የጀነቲክ ሀብቱ ወይም የማህበረሰብ ዕውቀቱ የተገኘበትን አካባቢ በምንጭነት የመጥቀስ፣

፲፭/ በአርክቦት የተገኘ የጀነቲክ ሀብትን ወይም የማህበረሰብ ዕውቀትን በመጠቀም ከሚገኘው ገቢ ላይ ለመንግሥትና ለሚመለከተው የአካባቢ ማህበረሰብ የማጋራት፣

፲፮/ የሀገሪቱን ሕጐች በተለይም የጤና፣ የደህንነት ሕይወትና የአካባቢ ጥበቃን በሚመለከት የወጡ ሕጐችን የማክበር፣

7/ submit to the Institute regular status reports of the research; and where genetic resource is collected repeatedly, follow up the environmental and socio-economic impact of the access and submit a report thereon;

8/ inform the Institute in writing of all the findings of the research and development based on the genetic resource and community knowledge accessed;

9/ not transfer the genetic resource and community knowledge accessed to any other third party or use same for any purpose other than that originally intended, without first notifying to and obtaining written authorization from the Institute;

10/ return any unused genetic material at the end of the planned research or upon termination of the access agreement;

11/ not transfer to third parties the access permit or the rights and obligations there under without obtaining the consent of the Institute to that effect;

12/ where he seeks to acquire intellectual property right over the genetic resources accessed or parts thereof, negotiate new agreement with the Institute based on the relevant laws of Ethiopia;

13/ not apply for a patent or any other intellectual property protection over the community knowledge accessed without first obtaining explicit written consent from the Institute;

14/ recognize the locality where the genetic resource or community knowledge accessed from as origin in the application for commercial property protection of the product developed there from;

15/ share the benefit that may be obtained from the utilization of the genetic resource or community knowledge accessed to the state and the concerned local communities;

16/ respect the laws of the country, particularly those relating to sanitary control, biosafety and protection of the environment;

፲፯/ የአካባቢ ማህበረሰቦችን ባሕላዊ ልምዶች፣ ባሕላዊ እሴቶችና ደንባቸውን የማክበር፣

፲፰/ የአርክቦት ውሉን ግዴታዎች የማክበር::

፲፰. ጥቅም መጋራት

፩/ በአርክቦት የተገኘ የጀነቲክ ሀብትን ወይም የማህበረሰብ ዕውቀትን በመጠቀም ከሚገኘው ገቢ ላይ መንግሥትና የአካባቢ ማህበረሰቦች የሚጋሩት የጥቅም ዓይነትና መጠን በሚፈረመው በእያንዳንዱ የአርክቦት ስምምነት የሚወሰን ይሆናል፣

፪/ በገንዘብ መልክ ከሚገኘው ጥቅም ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱/፩/ የተመለከተው የአካባቢው ማህበረሰብ ድርሻ ከተቀነሰ በኋላ የሚቀረው ገንዘብ የጀነቲክ ሀብትን ለመንከባከብና ለማበልጸግ እና የማህበረሰብ ዕውቀትን ለማስፋፋት ተግባር ይውላል:: ገንዘቡ ለዚህ ተግባር የሚውልበት ሀኔታ ኢንስቲትዩቱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፣

፫/ በመንግሥትና በሚመለከተው የአካባቢ ማህበረሰብ መካከል የሚኖረው በገንዘብ ያልሆነ የጥቅም መጋራት ከአርክቦት ባለፈቃዱ ጋር በሚደረገው የጥቅም ክፍፍል ላይ ተመሥርቶ በሚፈረመው የአርክቦት ስምምነት ውስጥ የሚገለጽ ይሆናል::

፲፱. የጥቅም ዓይነቶች

የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀትን ከማርከብ በመጋራት ሊገኘ የሚችለው ጥቅም የሚከተሉትን ሊጨምር ይችላል፣

፩/ የፍቃድ ክፍያ

፪/ የቅድሚያ ክፍያ፣

፫/ በየደረጃው የሚፈፀም ክፍያ፣

፬/ ሮያሊቲ፣

፭/ ለምርምር የሚውል የገንዘብ ክፍያ

፮/ የአእምሮ ንብረት የጋራ ባለቤት መሆን፣

፯/ የሥራ ዕድል፣

፰/ በአርክቦት በተገኘው የጀነቲክ ሀብት ወይም የማህበረሰብ ዕውቀት ላይ በሚደረገው ምርምር በኢንስቲትዩቱ ወይም አግባብነት ባለው ተቋም ውስጥ የሚሰሩ ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች መሳተፍ፣

17/ respect the cultural practices, traditional values and customs of local communities;

18/ observe the terms and conditions of the access agreement.

18. Benefit Sharing

1/ The kind and the amount of the benefit to be shared by the state and local communities from access to genetic resources or community knowledge shall be determined case by case in each specific access agreements to be signed.

2/ The remaining portion of the monetary benefit from access to genetic resources, after deducting the share of the local community as determined pursuant to Article 9 (1) of this Proclamation, shall be allocated for conservation of biodiversity and the promotion of community knowledge. The conditions how the money shall be put to such use shall be determmined by regulation;

3/ The sharing of non-monetary benefits from access to genetic resources among the state and the concerned local community shall be specified in each specific access agreement taking into account the kinds of benefits agreed to share with the access permit holder.

19. Types of Benefit

The benefit to be shared from an access to genetic resources and community knowledge may include the following modes:

1/ License fee;

2/ upfront payment;

3/ milestone payment;

4/ royalty;

5/ research funding;

6/ joint ownership of intellectual property;

7/ employment opportunity;

8/ participation of Ethiopian nationals from the Institute or the relevant institutions in the research based on the genetic resources or community knowledge accessed;

፱/ የጀነቲክ ሀብቱን በመጠቀም ምርት ለማምረት የሚያስፈልገውን የጀነቲክ ሀብት ጥሬ ዕቃ ለማቅረብ ቅድሚያ የማግኘት፣

፲/ የጀነቲክ ሀብትን ወይም የማህበረሰብ ዕውቀትን በመጠቀም የሚገኙ ምርቶችንና ቴክኖሎጂዎችን የማግኘት፣

፲፩/ የጀነቲክ ሀብትን የመጠበቅ፣ የመገምገም፣ የማበልፀግ፣ የማራባትና የመጠቀም ችሎታን ለማዳበር በተቋምና በአካባቢ ማህበረሰብ ደረጃ ሥልጠናን የማግኘት፣

፲፪/ የመሣሪያ፣ መሠረተ ልማትና የቴክኖሎጂ ድጋፍ የማግኘት፣ እና

፲፫/ እንደ አግባብነቱ የሚገኝ ማናቸውም ሌላ ጥቅም::

ክፍል አራት
ክትትል እና የማረሚያ እርምጃ

፳. ክ ት ት ል

፩/ ኢንስቲትዩቱ የአርክቦት ውል አፈጻጸምን በሚከተሉት መንገዶች ይከታተላል፣

ሀ/ በፍተሻ፣

ለ/ የአርክቦት ባለፈቃዶችና በጀነቲክ ሀብት አሰባሰብና ምርምር ላይ እንዲሳተፉና አርክቦትን እንዲቆጣጠሩ የተመደቡ ተቋሞች በየጊዜው በሚያቀርቡት የክንውንና የውጤት ሪፖርት፣

ሐ/ ማናቸውም ሰው ወይም ግለሰብ በሚያቀርበው ሪፖርት፣ እና

መ/ አግባብ ሆኖ በሚገኝ ማናቸውም ሌላ የመከታተያ መንገድ፣

፪/ በጀነቲክ ሀብት አሰባሰብና በምርምር ላይ እንዲሳተፉና የአርክቦት ውል አፈጻጸምን እንዲቆጣጠሩ የተሰየመ አግባብነት ያላቸው ተቋማት በተከናወነው የአሰባሰብና የምርምር እንቅስቃሴ በተገኘው ግኝትና በአርክቦት ውሉ አፈጻጸም ላይ በየወቅቱ ሪፖርት ለኢንስቲትዩት ማቅረብ አለባቸው፣

9/ priority to supply the raw material of genetic resource required for producing products there form;

10/ access to products and technologies developed from the use of genetic resource or community knowledge accessed;

11/ training, both at institutional and local communities levels, to enhance local skills in genetic resources conservation, evaluation, development, propagation and use;

12/ provision of equipment, infrastructure and technology support; and

13/ any other benefit as appropriate

PART FOUR
FOLLOW UP AND COMPLIANCE MEASURE

20. Follow-up

1/ The Institute shall follow-up the execution of access agreements through the following mechanisms:

a) Inspection;

b) periodic progress and status report by access permit holders and the relevant institutions designated to accompany the collection, participate in the research and monitor the implementation of access agreement;

c) A report by any other person or individual; and

d) Any other mechanism deemed appropriate

2/ The access permit holder and the relevant institutions designated to take part in the collection of and the research based on genetic resources accessed and to monitor the implementation of access agreements shall give periodic reports to the Institute on the collection conducted, the progress of the research and the findings there from.

፫/ ኢንስቲትዩቱ አርክቦት በተፈፀመበት የማህበረሰብ ዕውቀት ላይ የተካሄደው ምርምር የደረሰበትን ደረጃና የተገኘውን ውጤት የማህበረሰብ ዕውቀቱን አጠቃቀምና የተገኘውን የጥቅም መጋራት በተመለከተ ለሚመለከተው የአካባቢ ማህበረሰብ መረጃ መስጠት አለበት

፳፩. የማረሚያ ዕርምጃ

፩/ የጀነቲክ ሀብት አርክቦቱ በቀላሉ ሊመለስ የማይችል የጀነቲክ ሀብት መመናመን፣ የአካባቢ መራቆት ወይም የማህበረሰቦች ባሕላዊ እሴቶች መመናመን አደጋ የሚያስከትል ሆኖ ከተገኘ ኢንስቲትዩቱ የአርክቦት ውሉን መለወጥና የሚሰበሰበውን የጀነቲክ ሀብት መጠን መወሰን ወይም እንደ አግባብነቱ ማናቸውንም ሌላ ገደብ ማድረግ ይችላል፣

፪/ የአርክቦት ባለፈቃዱ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችን ወይም የአርክቦት ውሉን ግዴታዎች የጣሰ ወይም ሳያከብር የቀረ እንደሆነ ወይም አርክቦቱ በብዝሀ ሕይወት ሀብት ወይም በአካባቢ ላይ የውድመት አደጋ ካስከተለ ወይም ቅድሚያ በሚሰጣቸው የሕዝብ ጥቅሞች ላይ ጉዳት ካስከተለ ኢንስቲትዩቱ የአርክቦት ውሉን አግዶ ወይም አቋርጦ የጀነቲክ ሀብት ወይም የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦቱ እንዳይቀጥል መከልከል አለበት፣

፫/ ኢንስቲትዩቱ የአርክቦት ውልን የመለወጥ፣ የማገድ ወይም የማቋረጥ እርምጃ ሲወሰድ ውሳኔውን ለሚመለከተው የአካባቢ ማህበረሰብና ለአርክቦት ባለፈቃዱ መግለጽ አለበት::

ክፍል አምስት
የጀነቲክ ሀብት አሰሳ

፳፪. ክ ል ከ ላ

፩/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬/፪/ ድንጋጌ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ከኢንስቲትዩቱ የጀነቲክ ሀብት አሰሳ ፈቃድ የተሰጠው ካልሆነ በስተቀር ማናቸውም ሰው የጀነቲክ ሀብት አሰሳ ለማካሄድ አይችልም፣

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ድንጋጌ ቢኖርም የጀነቲክ ሀብትን ለመጠበቅ በሕግ ኃላፊነት የተሰጣቸው የመንግሥት አካላት ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ለሚያደርጉት የጀነቲክ ሀብት አሰሳ ከኢንስቲትዩቱ ፈቃድ ማግኘት አያስፈልጋቸውም ::

3/ The Institute shall inform the concerned local communities of the progress of the research and the findings therof, the utilization of community knowledge and the benefit shared there from.

21. Compliance Measure

1/ The Institute may alter an access agreement and limit the size of the genetic resource to accesse or put any other limitation, as appropriate, where it is recognized that the access has posed threat of genetic erosion, degradation of the environment or violation of the cultural values of communities which can not be easily averted.

2/ Where the access permit holder has violated or failed to comply with the provisions of this Proclamation or the terms and conditions of the access agreement or where the access causes risk of damage to genetic resources or the environment or affects overriding public interest, the Institute shall suspend or terminate an access agreement and prohibit the access to genetic resources or community knowledge;

3/ Where the Institute decides to alter, suspend or terminate an access agreement, it shall communicate same to the concerned local community and the access permit holder.

PART FIVE
EXPLORATION OF GENETIC RESOURCES

22. Prohibition

1/ Without prejudice to the provisions of Article 4(2) of this Proclamation, no person may conduct exploration of genetic resources unless in possession of exploration permit from the Institute.

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, organs of the state which are empowered by law to conserve genetic resources are not required to obtain exploration permit to conduct exploration of genetic resources in the discharge of their duties.

፳፫. ማመልከቻ ስለማቅረብ

፩/ የጀነቲክ ሀብት አሰሳ ፈቃድ ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ለኢንስቲትዩቱ የጽሑፍ ማመልከቻ ማቅረብ ይኖርበታል፣

፪/ ማመልከቻው የአሰሳውን ዓላማ፣ የሚታሰሰውን የጀነቲክ ሀብት ዓይነት አሰሳው የሚካሄድበትን አካባቢና አሰሳውን ለማካሄድ የታቀደበትን ጊዜ ማመልከት አለበት::

፳፬. የአሰሳ ፈቃድ ስለመስጠት

፩/ ኢንስቲትዩቱ የተሟላ የጀነቲክ ሀብት አሰሳ ማመልከቻ ሲቀርብለት፣ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ አግባብነት ካለው ተቋም ጋር በመመካከር፣ አመልካቹ የአሰሳ ፈቃድ ይሰጣል፣

፪/ የአሰሳ ፈቃዱ የሚታሰሰውን የጀነቲክ ሀብት ዓይነት አሰሳው የሚካሄድበትን አካባቢ፣ አሰሳው ሊካሄድ የታቀደበት የጊዜ ሰሌዳና ኢንስቲትዩቱ አስፈላጊ ናቸው የሚላቸው ሌሎች ሁኔታዎችን ማመልከት አለበት

፫/ ኢንስቲትዩቱ የአሰሳ ፈቃድ ለውጭ ሀገር ዜጋ በሚሰጥበት ጊዜ በአሰሳው ላይ አብረው እንዲገኙ ባለሙያዎቹን መመደብ ወይም አግባብነት ያለውን ተቋም መወከል አለበት::

፳፭. የአሳሾች ግዴታዎች

የአሰሳ ባለፈቃድ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩ በታል፣

፩/ የአሰሳ ፈቃዱን ቅጅ አሰሳው በሚካሄድበት አካባቢ ላለው ወረዳ አግባብነት ያለው አካል የመስጠት፣

፪/ በአሰሳ ፈቃዱ ውስጥ የተጠቀሱ ግዴታዎችን በሚገባ የማክበር፣

፫/ አሰሳው ሲጠናቀቅ ስለ አሰሳው ክንዋኔ ዝርዝርና የተሟላ ሪፖርት ለኢንስቲትዩቱ የማቅረብ፣

፬/ ጥያቄ በቀረበለት ጊዜ የአሰሳ ፈቃዱን የማሳየት፣

፭/ አሰሳው በሚካሄድበት አካባቢ ያለውን ባሕል፣ ልማድ፣ እሴት፣ የንብረት መብቶችና የሀገሪቱን ሀጐች የማክበር::

23. Application

1/ Any person who wants to obtain exploration permit shall present written application to the Institute.

2/ The application shall specify the purpose of the exploration, the types of the genetic resources to be explored, the locality where the exploration shall be conducted and the time schedule for the exploration.

24. Granting Exploration Permit

1/ Upon receiving a complete exploration application, the Institute shall, in consultation with the relevant institution where appropriate, grant an exploration permit to the applicant.

2/ The exploration permit shall specify the types of the genetic resources to be explored, the locality where the exploration shall take place, the time schedule of the exploration and any other condition which the Institute deems necessary.

3/ Where the Institute grants exploration permit to a foreigner, it shall assign its scientific personnel or designate other relevant institution to accompany the exploration mission.

25. Obligations of Explorers

Any holder of an exploration permit shall have the following obligations:

1/ deposit a copy of the exploration permit with the relevant institution in the district of the locality where the exploration will be conducted;

2/ strictly observe the terms and conditions specified in the permit;

3/ present to the Institute a detailed and complete report of the exploration mission upon its completion;

4/ show, up on request, the exploration permit issued to him;

5/ respect local customs, traditions, values, property rights in the locality where the exploration shall be conducted and the laws of the country.

ክፍል ስድስት
የአርክቦት አስተዳደር

፳፮. የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን

በዚህ አዋጅ ውስጥ የዱር እንስሳት ጀነቲክ ሀብትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች የማስፈፀም ሥልጣን የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ይሆናል::

፳፯. የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባር

በዚህ አዋጅ በሌሎች አንቀጾች የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

፩/ የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦት በዚህ አዋጅና ይህንን አዋጅ መሠረት በማድረግ በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መከናወኑን የማረጋገጥ፣

፪/ ከአርክቦት የሚገኙ ጥቅሞችን መቀበልና ለባለ ጥቅሙ እንዲደርስ የማድረግ፣

፫/ የአርክቦት ውል ሞዴሎችን የማዘጋጀት፣

፬/ የዚህን አዋጅ ይዘት ለሕዝብ የማስተዋወቅ፣

፭/ የጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት አርክ ቦት መረጃዎችን የመሰብሰብ፣ የማጠናቀር፣ የመተንተንና እንደአስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎች የማሠራጨት፣

፮/ ይህንን አዋጅ በመተላለፍ በሚፈፀሙ የወንጀል ተግባሮች ላይ ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ የማድረግ፣

፯/ ይህንን አዋጅ በተግባር ለማዋል አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን የማውጣትና ሌሎች አስፈላጊ ተግባራትን ማከናወን፣

፰/ ተግባሩን በተሻለ መንገድ ለማካሄድ አስፈላጊና አመቺ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ሥልጣንና ተግባሩን በሕግ ለተቋቋመ አካል በውክልና የመስጠት::

፳፰. የአካባቢ ማህበረሰቦች ኃላፊነት

የአካባቢ ማህበረሰቦች

፩/ የማህበረሰቡ አባል ያልሆነ ማናቸውም ሰው ፈቃድ ሳይኖረው የጀነቲክ ሀብት ከአካባቢው እንዳይሰበሰብና እንዳይወሰድ የመከልከል፣ እና

PART SIX
ADMINISTRATION OF ACCESS

26. Powers of Ministry of Agriculture and Rural development

The implementation of the provisions of this proclamation that deal with genetic resources of wild animals shall be the responsibility of the Ministry of Agriculture and Rural Development.

27. Powers and Duties of the Institute

Without prejudice to the powers and duties entrusted to it in other provisions of this Proclamation, the Institute shall have the powers and duties to:

1/ Follow-up and ensure that access is carried out in accordance with this Proclamation as well as regulations and directives issued hereunder;

2/ collect the benefits to be obtained from access agreements and pass over to beneficiaries;

3/ prepare model access agreements;

4/ sensitize contents of this Proclamation;

5/ collect, analyze and as necessary disseminate to users information on access to genetic resources and community knowledge;

6/ cause that legal actions be taken against offences committed in violations of this Proclamation;

7/ issue directives and perform such other activities necessary for the implementation of this Proclamation;

8/ delegate its powers and duties to other legally established bodies where deemed necessary and convenient to carry out its duties in a better way.

28. Responsibilities of Local Communities

Local communities shall have the responsibility to:

1/ prohibit any person, who does not belong to their communities, from collecting or taking genetic resources from their localities without having the necessary permit; and

፪/ የማህበረሰቡ አባል ያልሆነ ማናቸውም ሰው የጀነቲክ ሀብት ከአካባቢው ሲሰበሰብ ወይም ሰብስቦ ይዞ ሲሄድ ፈቃድ ያለው መሆኑን የመጠየቅና ፈቃድ የሌለው ከሆነ ወዲያውኑ በአቅራቢያው ለሚገኝ የቀበሌ ወይም የወረዳ መስተዳድር የማሳወቅ ወይም ወደነዚሁ እንዲቀርብ የማድረግ፣

ኃላፊነት አለባቸው::

፳፱. የክልል መስተዳድር አካላት ኃላፊ

የቀበሌ መስተዳድሮችና በየደረጃው የሚገኙ የጀነቲክ ሀብት ጥበቃ የሚመለከታቸው የክልል መስተዳድር አካላት፣

፩/ የአካባቢው ማህበረሰብ አባል ያልሆነ ማናቸውም ሰው ፈቃድ ሳይኖረው የጀነቲክ ሀብት ከክልላቸው እንዳይሰበሰብና እንዳይወሰድ የመቆጣጠር፣ እና

፪/ የአካባቢው ማህበረሰብ አባል ያልሆነ ማናቸውም ሰው የጀነቲክ ሀብት ሲሰበሰብ ወይም ሰብስቦ ይዞ ሲሄድ ይህንን ለማድረግ ፈቃድ የያዘ መሆኑን መጠየቅና ፈቃድ የሌለው ከሆነ የሰበሰበውን ጀነቲክ ሀብት በመያዝ ለሕግ እንዲቀርብ የማድረግና የተያዘውን የጀነቲክ ሀብት ዓይትና ይዞ የተገኘውን ሰው ማንነት ለኢንስቲትዩቱ በዝርዝር የማሳወቅ፣

ኃላፊነት አለባቸው::

፴. የጉምሩክ ባለሥልጣኖች ኃላፊነት

የጉምሩክ ባለሥልጣኖች ከኢንስቲትዩቱ በሚሰጣቸው መመሪያ መሠረት የሚከተሉትን የመፈጸም ኃላፊነት ይኖርባቸዋል፣

፩/ ከሀገሪቱ የሚወጣ የጀነቲክ ሀብት የመውጫ ፈቃድ ከኢንስቲትዩቱ የተሰጠበት መሆኑን የመቆጣጠር፣

፪/ የጀነቲክ ሀብት የሚያጓጉዝ ወይም የያዘ ከሀገር የሚወጣ ማናቸውም ሰው ከኢንስቲትዩቱ የተሰጠውን የጀነቲክ ሀብት ከሀገር የማስወጫ ፈቃድ እንዲያሳይ የመጠየቅ፣

፫/ አስፈላጊው ፈቃድ ሳይኖር ከሀገር በመውጣት ላይ የሚገኝ የጀነቲክ ሀብትንና የጀነቲክ ሀብቱን ከሀገር በማስወጣት ላይ የሚገኝን ሰው መያዝና ወዲያውኑ በአካባቢው ለሚገኝ አግባብነት ላለው አካልና ለኢንስቲትዩቱ የማሳወቅ፣

2/ require any person, who does not belong to their communities and who is collecting or taking genetic resource from their localities, to show his access permit, and if he is without permit immediately notify or present him to the nearest kebele or wereda administration.

29. Responsibilities of Regional Bodies

Kebele administration and regional bodies at all levels responsible for the conservation of genetic resources shall:

1/ regulate that genetic resources is not accessed from their respective jurisdiction without permit by any person who does not belong to the communities thereof; and

2/ require access permit from any person, who does not belong to the communities thereof and who is collecting or taking genetic resources from their respective jurisdiction, and if he is without permit, seize the genetic resource and present him to the law and notify the Institute the detailed particulars of the genetic resource and the person found in possession of same.

30. Responsibility of Customs Officers

In accordance with directives to be given to them by the Institute, customs officers shall have the responsibilities to:

1/ inspect that any genetic resources being taken out of the country has been accompanied with an export permit given by the Institute;

2/ require any person leaving the country who is transporting or is in possession of genetic resource to produce the necessary permit to this effect from the Institute;

3/ seize genetic resource being transported out of the country and the person transporting same without permit from the Institute and immediately report same to the nearby relevant body and the Institute;

፬/ ወደ ውጭ ሀገር በሚላክ የጀነቲክ ሀብት ምርት መያዣ ላይ በምርቱ ውስጥ የሚገኘውን የጀነቲክ ሀብት መጠቀም የተከለከለ መሆኑንና ተጠቅሞ መገኘትም በሕግ የሚያስቀጣ ድርጊት መሆኑን የሚገልጽ ቃል የተፃፈበት መሆኑን የማረጋገጥ::

4/ Ensure that a statement is written on the package of a biological resource product to be exported indicating that the use of the genetic material contained in the product is prohibited and doing so would constitute a penal offence.

፴፩. የመልዕክት አስተላላፊ ድርጅቶች ኃላፊነት

የፖስታና ሌሎች የፈጣን መልዕክት አስተላላፊ ድርጅቶች የጀነቲክ ሀብትን በመልዕክትነት ከኢትዮጵያ ውጪ ለመላክ ከመቀበላቸውና ከመላካቸው በፊት ደንበኞቻቸው የጀነቲክ ሀብትን ከሀገር ለማስወጣት ከኢንስቲትዩቱ የተሰጣቸውን ፈቃድ እንዲያቀርቡ መጠየቅ አለባቸው::

31. Responsibilities of Mail Service Institutions

Postal and other courier service institutions shall, before receiving and transporting genetic resources out of the country as mail, require their clients to produce permit from the Institute to export the genetic resources out of the country.

፴፪. የኳራንቲን ተቆጣጣሪ መሥሪያ ቤቶች ኃላፊነት

የኳራንቲን ተቆጣጣሪ መሥሪያ ቤቶች ለሕይወታዊ ሀብት ምርት የሚሰጡት የኳራንቲን ሰርተፊኬት በሕይወታዊ ሀብቱ ውስጥ የሚገኝን የጀነቲክ ሀብት ለመጠቀም የሚያስችል ፈቃድ አለመሆኑንና በኳራንቲን ሰርተፊኬቱ ብቻ በሕይወታዊ ሀብቱ ውስጥ የሚገኝን የጀነቲክ ሀብት መጠቀም የተከለከለና ወንጀል መሆኑን የሚገልጽ ቃል እንዲይዝ ማድረግ አለባቸው::

32. Responsibilities of Quarantine Control Institutions

Quarantine control Institution shall, ensure that the quarantine certificate they issue to biological resource products, contain a statement indicating that the certificate does not constitute a permit to use the product as genetic resource and that doing so is prohibited and would constitute an offence.

ክፍል ሰባት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

PART SEVEN
MISCELLANEOUS PROVISIONS

፴፫. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

፩/ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የተደረጉ የአርክቦት ውሎች መከለስና ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር እንዲጣጣሙ መደረግ አለባቸው::

33. Transitory Provisions

1/ Access agreements made prior to the coming into force of this Proclamation shall be revised and harmonized with the provisions of this Proclamation.

፪/ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የተደረጉ የአርክቦት ውሎች እስከሚከለሱና ከዚህ አዋጅ ጋር እንዲጣጣሙ እስከሚደረጉ ድረስ ከመፈፀም ታግደው ይቆያሉ::

2/ The access to gentic resources under agreements consluded prior to the coming into force of this Proclamation shall be suspended until they are revised and harmonized with the provisions of this Proclamation.

፴፬. የመተባበር ግዴታ

ለዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት ለሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች አፈጻጸም ማናቸውም ሰው ከኢንስቲትዩቱ፣ አግባብነት ካላቸው ተቋማትና ከሚመለከታቸው የአካባቢ ማህበረሰቦች ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት::

34. Duty to Cooperate

Any person shall have the duty to cooperate with the Institute, the relevant institutions, and local communities in the implementation of this Proclamation as well as regulations and directives issued hereunder.

፴፭. ቅ ጣ ት

፩/ ማናቸውም ሰው፣

ሀ/ ከኢንስቲትዩቱ የአርክቦት ፈቃድ በቅድሚያ ሳያገኝ የጀነቲክ ሀብት ወይም የማህበረሰብ ዕውቀትን ያረከበ፣

ለ/ በአርክቦት ማመልከቻ ውስጥ ወይም የአርክቦት ውል አፈጻጸም ክትትል ወቅት የሀሰት መረጃ የሰጠ፣

ሐ/ ከኢንስቲትዩቱ ፈቃድ ሳያገኝ በአርክቦት ውሉ ውስጥ የተጠቀሰውን የአርክቦት ዓላማ የለወጠ፣

መ/ የአሰሳ ፈቃድ በቅድሚያ ከኢንስቲትዩቱ ሳያገኝ የጀነቲክ ሀብት አሰሳ ያካሄደ ወይም የአሰሳ ፈቃድ ማመልከቻ ውስጥ የሀሰት መረጃ የሰጠ ከሆነ፣

ያረከበው የጀነቲክ ሀብት መወረሱና የተሰጠው ፈቃድ መሠረዙ እንደዚሁም ፍትሐብሔር ረገድ የሚኖርበት ኃላፊነት ሳይቀር እንደነገሩ ሁኔታ ከ፫ ዓመት በማያንስ ጽኑ እሥራትና ከብር አስር ሺህ እስከ ሰላሳ ሺህ ሊደርስ በሚችል መቀጮ ይቀጣል::

፪/ ድርጊቱ የተፈፀመው ብርቅዬ የጀነቲክ ሀብትን በሚመለከት የሆነ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ ከአምስት ዓመት በማያንስ ጽኑ እሥራትና ከሃምሳ ሺህ ብር እስከ አንድ መቶ ሺህ ብር ሊደርስ በሚችል መቀጮ ይቀጣል::

፫/ በዚህ አንቀጽ የተመለከቱት ድርጊቶች የተፈፀሙት በቸልተኝነት የሆነ እንደሆነ ቅጣቱ ከአምስት ሺህ ብር የማያንስ መቀጮ ወይም እንደነገሩ ሁኔታና እንደወንጀሉ ከባድነት ከሦስት ወር የማያንስ ቀላል እሥራት ይሆናል::

፴፮. ተፈጻሚ የማይሆኑ ሕጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም::

35. Penalty

1/ Any person who:

a) Accesses genetic resources or community knowledge without obtaining an access permit from the Institute;

b) Provides false information in the access application or in the course of subsequent monitoring of access agreement;

c) Subsequently changes the purpose of access specified in the access agreement without obtaining permit from the Institute to the effect.

d) Explores genetic resources without obtaining exploration permit from the Institute or provides false information in the application for exploration permit;

Shall, with out prejudice to the confiscation of the genetic resource accessed, the cancellation of the access permit granted, and the civil liability arising thereof, be punished, depending on the gravity of the circumstance, with reigorous imprisonment of not less than three years and a fine of not less than ten-thousand and not exceeding thrity-thousand birr.

2/ Where the offence committed is in relation to genetic resources endemic to Ethiopia:-
The punishment shall be, depending on the circumstance, rigorous imprisonment of not less than five years and not exceeding twelve-years and a fine ranging from fifty thousand birr to hundred-thousand birr.

3/ Where the offences under this Article are committed in negligence, the penalty shall be a fine of not less than five thousand birr or, depending on the circumstance and the gravity of the offence, simple imprisonment of not less than three months.

36. Inapplicable Laws

No law, regulation, directive or practice shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, have effect with respect to matter provided for by this Proclamation.

ሻኗ. ደንብ የማውጣት ሥልጣን

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ በሚገባ ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችን ማውጣት ይችላል::

ሻኟ. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ የካቲት ፳ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም.

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

37. Power to Issue Regulations

The Council of Ministers may issue regulations necessary for the proper implementation of this Proclamation.

38. Effective Date

This Proclamation shall come in to force upon publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 27th day of February, 2006

GIRMA WOLDEGIORGIS

PRESIDENT OF THE FEDERA DEMOCRATICREPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት